# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# ስፖርት ምክር ቤት

# መቋቋሚያና መተዳደሪያ

# ተሻሽሎ የወጣ

# መመሪያ

# ቁጥር 10/2015

2015ዓ.ም
አዲስ አበባ

# መግቢያ

የሀገራችንን ስፖርት በህዝባዊ አደረጃጀትና አሰራር ለማጠናከርና ለመምራት እንዲያስችል የኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲ በ1990 ዓ.ም ፀድቆ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረትም ከመንግስት ጎን ሆነው የስፖርቱን ህዝባዊነት፣ አደረጃጀትና አመራር የማገዝና የማጠናከርን ሚና የሚወጡት የስፖርት ምክር ቤቶችና የስፖርት ማህበራት እንደሆኑ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

እንደሚታወቀው ከዚህ በፊት በከተማው አስተዳደር ተቋቁመው በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙ ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶች ቢኖሩም በአደረጃጀትና በአመራር ያልተጠናከሩና በሚፈለገው ልክ ባለመደራጀታቸው  በልዩ ልዩ አገልግሎቶች የመንግስት ድጋፍ ያልተለያቸው ሆነዋል፡፡

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 74/2014 መሰረት የስፖርት ምክር ቤቶችን የማቋቋምን ስልጣን ለአዲስ አበባ ስፖርት ኮሚሽን የሰጠ በመሆኑ የከተማውን አስተዳደር ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶችን በየደረጃው በማጠናከር በከተማው አስተዳደር ለሚቋቋሙ ስፖርት ምክር ቤቶች መቋቋሚያና መተዳደሪያ መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በማግኘቱ ይህን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ምክር ቤት መቋቋሚያና መተዳደሪያ መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## 1. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1.1. መቋቋም

1.1.1. ከዚህ ቀጥሎ ምክር ቤት ተብሎ የሚጠራውና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርትን በበላይነት የሚመራ የስፖርት ምክር ቤት ተቋቋሟል፤

1.1.2. በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ የስፖርት ምክር ቤቶች ይቋቋማሉ፤

### 1.2. አውጪው ባለስልጣን

1.2.1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶችን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 ለቢሮው በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

### 1.3. አጭር ርዕስ

1.3.1. ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስፖርት ምክር ቤት መቋቋሚያና መተዳደሪያ መመሪያ ቁጥር 10/2015 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1.4.ትርጓሜ፡

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1.4.1. "**ስፖርት**"፡- ማለት በኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲ መሰረት ማንኛውም ግለሰብ አቅሙ በፈቀደ መጠን በግሉ ወይም በጋራ በተደራጀና ባልተደራጀ መልክ የሚከናወኑ የተለያዩ የአካል እንቅስቃሴዎች ሆኖ የስፖርት ስልጠናዎችንና ውድድሮችን ያጠቃልላል፡፡

1.4.2. "**የከተማ አስተዳደር**"፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

1.4.3. "**ቢሮ**" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርቱን በበላይነት እንዲመራ በአዋጅ ስልጣን የተሰጠው ተቋም ማለት፡፡

1.4.4. "**ስፖርት ምክር ቤት**"፡- ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በመመሪያ ቁጥር 007/2014 የተቋቋመ ም/ቤት ነው፡፡

1.4.5. "**የስፖርት ማህበር**"፡- ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እውቅና አግኝቶ በፌዴሬሽን፣ በአደራጅ ኮሚቴ፣ በስፖርት ኮሚቴ፣ በአሶሴሽን ደረጃ የተቋቋመና አንድን ስፖርት በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ለመምራትና ለማስፋፋት ኃላፊነት የተሰጠው የስፖርት ማህበር ነው፡፡

1.4.6. "**ፌዴሬሽን**" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እውቅና አግኝቶ የተቋቋመና አንድን ስፖርት በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ለመምራትና ለማስፋፋት ኃላፊነት የተሰጠው የስፖርት ማህበር ነው

1.4.7. "**የስፖርት ኮሚቴ**" ማለት አንድን የስፖርት ዓይነት ከአንድ በላይ የስፖርት ዓይነቶችን በወከሉት የህብረተሰብ ክፍል ለማስፋፋት፣ ለመምራት፣ ለማስፈፀምና አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ የስፖርት ማህበር ነው፡፡

1.4.8. "**የስፖርት አደራጅ ኮሚቴ**" ማለት አንድ ስፖርት ለመምራት የፌዴሬሽንን አቅም እስኪያሟላ ድረስ የተቋቋመ የስፖርት ማህበር ነው፡፡

1.4.9. "**የስፖርት አሶሴሽን**"፦ ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እውቅና አግኝቶ በተቋቋመበት የስፖርት ዓይነት በከተማ አስተዳደሩ ለመምራትና ለማስፋፋት ኃላፊነት የተሰጠው የስፖርት ማህበር ነው፡፡

1.4.10. "**የስፖርት ክለብ**"፦ ማለት የስፖርት እንቅስቃሴን ለማራመድ በአዲስ አበባ ስፖርት ኮሚሽን እውቅና አግኝቶ የተቋቋመ የስፖርት ቡድን ነው፡፡

1.4.11. "**አባላት**"፦ ማለት የስፖርት ምክር ቤት አባል የሆነና በስፖርት ማህበራት የታወቁ የስፖርት ድርጅቶች ተወካይ ግለሰቦች ናቸው፡፡

## 1.5. የተፈፃሚነት ወሰን

15.1. ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ባሉ የስፖርት ምክር ቤቶች የስፖርት ማህበራት ግለሰቦችና የምክር ቤቱ አባላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 1.6. የምክር ቤቱ ዓላማዎች

1.6.1 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ስፖርት እንዲስፋፋ በማድረግ የከተማዋን ነዋሪዎች በተለያዩ የስፖርት እንቅስቃሴዎች የሚያደርጉትን ተሳትፎ ማጎልበት፣

1.6.2 ከህብረተሰብ የስፖርት ተሳትፎ በመነሳት ከተማዋንና አገርን ሊወክሉ የሚችሉ ምርጥ እና ተተኪ ስፖርተኞችን ማፍራት፣

1.6.3 ስፖርትን በሚመለከት ከተለያዩ አካላት ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር ስፖርቱ ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው ማስቻል፣

1.6.4 የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በአግባቡ እንዲያዙ፡ እንዲጠበቁና እንዲገነቡ በማድረግ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ፣

1.6.5 የከተማዋን ስፖርት ከሌሎች የአህጉርና መሰል እህት ከተሞች ጋር የማቀራረብ፣ በስፖርት ውድድር፣ ስልጠናና የስፖርት መሰረተ ልማት ግንባታ ዙርያ የልምድና ተሞክሮ ልውውጥ ማድረግ፣

1.6.6 የከተማዋን ስፖርት እንቅስቃሴ ለማሳደግ የሚያስችል የሀብት አሰባሰብ ስርዓት በመዘርጋት ደረጃ በደረጃ ስፖርቱ ከመንግስት ድጎማ ነፃ እንዲወጣ የማስቻል አሰራር ማጎልበት፣

## 1.7 ፅህፈት ቤት

1.7.1 ምክር ቤቱ የራሱ ጽ/ቤትና እንደአስፈላጊነቱ የራሱ ሰው ኃይል ይኖረዋል፡፡ ይሁን እንጂ በሂደት የራሱ ፅ/ቤት እስኪኖረው ድረስ ቢሮው የምክር ቤቱ ፅ/ቤት በመሆን ያገለግላል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2. የከተማ ስፖርት ምክር ቤት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር

### 2.1. የከተማ ስፖርት ምክር ቤት አወቃቀር

2.1.1. ጠቅላላ ጉባኤ

2.1.2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

2.1.3. ኦዲት ኮሚቴ ናቸው

### 2.2. የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ አባላት

2.2.1. **በድምጽ የሚሳተፉ የስፖርት ም/ቤቱ ጉባኤ አባላት**

2.2.1.1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ -------------------------------------- ሰብሳቢ

2.2.1.2. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ -------------------------- ም/ሰብሳቢ

2.2.1.3. የአ/አ/ከ/አስ/ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የስፖርት ዘርፍ ም/ቢሮ ኃላፊ ----- ፀሐፊ

2.2.1.4. የአ/አ/ከ/አስ/የስራ ኢንተርፐራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ ------ አባል

2.2.1.5. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቨስና የሰዉ ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ --- አባል

2.2.1.6. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ---------------------- አባል

2.2.1.7. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ ---------------- አባል

2.2.1.8. የአ/አ/ከ/አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ --------------- አባል

2.2.1.9. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ ----------------- አባል

2.2.1.10. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኃላፊ --------------- አባል

2.2.1.11. የአ/አ/ከ/አስ/ቴክኒክ ሙያና ስልጠና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ ------ አባል

2.2.1.12. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ኃላፊ ------------------------ አባል

2.2.1.13. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ ------------------------- አባል

2.2.1.14. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ----------------- አባል

2.2.1.15. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ------ አባል

2.2.1.16. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ------------ አባል

2.2.1.17. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ------------------------------------ አባል

2.2.1.18. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ዉበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ኃላፊ ---------------- አባል

2.2.1.19. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ----------------------------- አባል

2.2.1.20. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ኮሚኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ -------------------------------- አባል

2.2.1.21. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ ---------------------------- አባል

2.2.1.22. የአስራ አንዱንም ክፍለ ከተማ ስፖርት ም/ቤት ሰብሳቢዎች ------------ አባል

2.2.1.23. የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት --------------------------------- አባል

2.2.1.24. የአ/አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት ------------------------------------------- አባል

2.2.1.25. የአዲስ አበባ አካል ጉዳተኞች ማህበር ሊቀመንበር ----------------------- አባል

2.2.1.26. የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር ሊቀመንበር ----------------------------- አባል

2.2.1.27. የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ------------------------------- አባል

2.2.1.28. የአዲስ አበባ ሰራተኞች ማህበር ሊቀመንበር ------------------------------ አባል

2.2.1.29. የስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር ሰብሳቢ -------------------------------------- አባል

2.2.1.30. የአዲስ አበባ ወጣቶች ፌዴሬሽን ሰብሳቢ ---------------------------------- አባል

2.2.1.31. የአዲስ አበባ ሴቶች ፌዴሬሽን ሰብሳቢ--------------------------------------- አባል

2.2.1.32. የ/አበባ እድሮች ም/ቤት ሰብሳቢ---------------------------------------------- አባል

2.2.1.33. የስፖርት ም/ቤቱ አስተዳደር ኃላፊ ------------------------------------------ አባል

2.2.1.34. የቢሮ ክፍያና ሒሳብ ዳይሬክተር-------------------------------------------- አባል

2.2.1.35. የስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክተር --------------------- አባል

2.2.1.36. የስፖርት ትምህርትና ስልጠና ዳይሬክተር---------------------------------- አባል

2.2.1.37. የማህበረሰብ ስፖርት ማስፋፊያና ተሳትፎ ዳይሬክተር ------------------- አባል

2.2.1.38. የማዕከላትና ማዘውተሪያ ስፍራዎች ልማትና አስተዳደር ዳይሬክተር --- አባል

2.2.1.39. በአ/አ/ወጣ/ስፖ/ቢሮ የትምህርትና ሥልጠና ማዕከላት ስራ አስኪያጆች -------- አባል

2.2.2. **ያለድምጽ የሚሳተፉ የጉባኤ አባላት**

2.2.2.1. የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ደጋፊ ዳይሬክቶሬቶች

2.2.2.2. የአስራ አንዱም ክፍለ ከተማ ስፖርት ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣

2.2.2.3. የአስራ አንዱም ክፍለ ከተማ የስ/ማ/ማ/ውድድር ቡድን መሪዎች፣

2.2.2.4. የአ/አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ቡ/መሪዎችና ትምህርትና ስልጠና ማዕከላት ቡ/መሪዎችና

2.2.2.5. በከተማዋ ስፖርት እንቅስቃሴ የላቀ አስተዋጽኦ ያደረጉ ግለሰቦችና የተቋማት ተወካዮች፣

2.2.2.6. የስፖርት ማህበራት ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ቴክኒክ ባለሙያዎች

2.2.2.7. የከተማዋ የህትመትና ኤሌክትሮኒክስ የሚዲያ ተቋማት ተወካዮች

2.2.2.8. የሙያ ማህበራት

## 2.3. የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

2.3.1. የከተማው አስተዳደሩን ስፖርት በበላይነት ይመራል፣

2.3.2. የምክር ቤቱን ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቋቁማል፣ አባላቱንም ይሰይማል፣ አባላቱ ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ ውሳኔ ይሰጣል፤

2.3.3. የክፍለ ከተማና የወረዳ ስፖርት ም/ቤቶች እንዲቋቋሙ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

2.3.4. በስሩ አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ተግባር ይሰጣል፣

2.3.5. ልዩ ልዩ የውስጥ መመሪያዎችን ያወጣል፣ በስራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፣

2.3.6. ለስፖርት ምክር ቤቱ የኦዲት ኮሚሽንን ይሰይማል፣

2.3.7. ለስፖርት ዕድገት መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ የበላይ አካል ውሳኔ የሚጠይቁ ጉዳዮችን አጥንቶ ለከተማው አስተዳደር የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣

2.3.8. በመኖሪያ አካባቢ፣ በትምህርት ተቋማትና በመስሪያ ቤቶች የሚካሄደውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት እንቅስቃሴን እየገመገመና እያጠና የሚዳብርበትን ሁኔታ ይቀይሳል፣

2.3.9. በሀገር አቀፍ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶት በከተማችንም እየተተገበረ ያለውን የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ልማት ስልጠና ፕሮግራምንለማሳደግ ይሰራል፣

2.3.10. የከተማዋ ነዋሪዎች በስፖርት ለሁሉምና ባህላዊ ስፖርቶች እንዲሳተፉ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣

2.3.11. አካል ጉዳተኞችና ሴቶች በስፖርት እንዲሳተፉ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

2.3.12. የከተማው ባለሃብት በስፖርት ዘርፍ ኢንቨስት እንዲያደርጉ በማዘውተሪያ ስፍራዎች ግንባታ፣ በስፖርት አካዳሚ ምስረታና በስፖርት ትጥቅና መሳርያዎች የማምረት ተግባር ላይ እንዲሰማሩ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

2.3.13. የህብረተሰቡ የስፖርት ግንዛቤ እንዲዳብር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፣

2.3.14. የስፖርት ጥናትና ምርምር ስራዎች እንዲበረታቱ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

2.3.15. በከተማ አስተዳደሩ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲስፋፉ፣ እንዲጠበቁና እንዲገነቡ ተገቢውን ይፈፅማል፣

2.3.16. ለስፖርቱ መስፋፋት የሚረዱ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

2.3.17. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠቃለው የሚቀርቡትን የከተማ አስተዳደሩን የስፖርት ዓመታዊ የስራ እቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል፣

2.3.18. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠቃለው የሚቀርቡለትን የአስተዳደሩን ስፖርት የስራ ክንውንና የፋይናንስ ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፣

2.3.19. በስፖርት ዙሪያ የሚነሱ ችግሮችን መርምሮ መፍትሄ ይሰጣል፣

2.3.20. የም/ቤቱንና የፌዴሬሽኖችን የፋይናንስ መመሪያን ያወጣል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

2.3.21. በገቢ ምንጮቹ አማካይነት የተገኘውን ገንዘብና ንብረት ያስተዳድራል፡፡

## 2.4. የስፖርት ም/ቤት ስብሰባ ስነ-ስርዓት

2.4.1. ምክር ቤቱ በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፣

2.4.2. የም/ቤቱ የስብሰባ ቀንና ቦታ መግለጫ፣ ያለፈው ቃለ-ጉባዔና የመወያያ አጀንዳዎች ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር ከስብሰባው ሶስት ቀን በፊት ለአባላቱ ይደርሳል፣

2.4.3. በምክር ቤቱ ስብሰባ ወቅት በድምፅ ከሚሳተፉት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሆኑ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው ይሆናል፣

2.4.4. በምክር ቤቱ ስብሰባ ወቅት መገኝት ከሚገባቸው ከግማሽ በታች ከሆነ የዕለቱ ስብሰባ ሌላ ተቀያሪ ቀን መርጦ በተገኙ አባላት ጉባኤውን የሚያካሂድ ይሆናል፣

2.4.5. አጠቃላይ ውሳኔን የሚጠይቁ ጉዳዩች ማለትም የውስጥ መመሪያዎችን ማጽደቅ፣ ዕቅድና በጀት ማፅደቅ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ ጉዳዮች በሚቀርብበት ጊዜ ቢያንስ $50^{+1}$ አባላት መገኘት አለባቸው፣

2.4.6. የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የሚፀድቀው በድምጽ ብልጫ ሆኖ ለሁሉም ግልጽ በሆነ የድምጽ አሰጣጥ መንገድ ነው፣

2.4.7. በአንድ ጉዳይ ላይ በሚሰጥ ድምጽ አሰጣጥ የተሰጠው ድምጽ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው አሸናፊ ይሆናል፣

## 2.5. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

2.5.1. በማንኛውም ስፍራ የምክር ቤቱ ህጋዊ ተጠሪ ነው፣

2.5.2. የምክር ቤቱን ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ይመራል፣

2.5.3. በምክር ቤቱ ስብሰባ ወቅት ድምጽ እኩል ከተከፈለ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣

2.5.4. የምክር ቤቱን ስብሰባ አጀንዳዎች ከፀሐፊው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣

2.5.5. የምክር ቤቱ ዕቅድና በጀት እንዲሁም የዕቅድ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርት መዘጋጀቱን ያረጋግጣል በበላይነት ይመራል፣

2.5.6. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣

2.5.7. የምክር ቤቱን ጠቅላላ ስራዎች ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

## 2.6. የምክር ቤቱ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

2.6.1. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሰራል፣

2.6.2. ከም/ቤቱ ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፣

**2.7. የምክር ቤቱ ፀሐፊ ስልጣንና ተግባር**

2.7.1. ከምክር ቤቱ ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢ ጋር በመሆን የስብሰባ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፣

2.7.2. የምክር ቤቱን ዕቅድና በጀት እንዲሁም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ያዘጋጃል፣

2.7.3. የምክር ቤቱ ስብሰባዎች ቃለ-ጉባኤ እንዲያዝ ያደርጋል፣

2.7.4. የምክር ቤቱ ልዩ ልዩ ሰነዶች በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፣

2.7.5. በምክር ቤቱ ሰብሳቢ በሚሰጠው ውክልና መሰረት የፅሁፍ ልውውጦችን ያደርጋል፣

2.7.6. ለምክር ቤቱ አባላትና ለሚመለከታቸው አካላት የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፣ አሰፈላጊ ሰነዶችንም ለአባላቱ ያሰራጫል፣

2.7.7. የምክር ቤቱን መሰብሰቢያ አዳራሽ እንዲዘጋጅ ያደርጋል አስፈላጊ ሁኔታዎችም መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣

**2.8. የምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ <u>የሚከተሉት ናቸው</u>**

2.8.1. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ -------------------------- ሰብሳቢ

2.8.2. የአ/አ/ከ/አስ/ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የስፖርት ዘርፍ ም/ቢሮ ኃላፊ ------- ም/ሰብሳቢ

2.8.3. የስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክቶሬት---------------------- ጸሀፊ

2.8.4. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ------------------------ አባል

2.8.5. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ ------------------ አባል

2.8.6. የአ/አ/ከ/አስ/ቴክኒክ ሙያና ስልጠና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ ---------- አባል

2.8.7. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ኃላፊ ---------------------------- አባል

2.8.8. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ------------------------- አባል

2.8.9. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ ----------------------------- አባል

2.8.10. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ---------------- አባል

2.8.11. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ -------- አባል

2.8.12. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ -------------- አባል

2.8.13. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የክፍያና ሒሳብ ዳይሬክተር-- አባል

2.8.14. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ግ/ን/አስተዳደር ዳይሬክተር--- አባል

2.8.15. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ዕቅድ ዝ/ክ/ግ/ዳይሬክተር ---- አባል

2.8.16. የአ/አ/ከ/አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ቴ/አማካሪ -------------------- አባል

2.8.17. የ4 ስፖርት ማህበራት ፕሬዝዳንቶች ---------------------------------------- አባል

2.8.18. የስፖርት ትምህርትና ስልጠና ዳይሬክተር------------------------------------ አባል

2.8.19. የማህበረሰብ ስፖርት ማስፋፊያና ተሳትፎ ዳይሬክተር --------------------- አባል

2.8.20. የማዕከላትና ማዘውተሪያ ስፍራዎች ልማትና አስተዳደር ዳይሬክተር ----- አባል

## 2.9. የምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

2.9.1. በምክር ቤቱ የሚወጡ መመሪያዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣

2.9.2. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል ያስፈፅማል፣

2.9.3. በቢሮው አማካይነት ተዘጋጅተው የሚቀርቡትን ዓመታዊ እቅድና በጀት እንዲሁም የእቅድ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት መርምሮ ለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ሲፀድቅም በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣

2.9.4. ከስፖርት ም/ቤቱ በጀት በዝውውር ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራት በፅ/ቤቱ ሲቀርብ መርምሮ እንዲዘዋወር ያስተናግዳል፣

2.9.5. ከፅ/ቤቱና ከስፖርት ማህበራት ጋር በመሆን ከተማ አቀፍና ሀገር አቀፍ የስፖርት ውድድሮችንና ፌስቲቫሎችን ያዘጋጃል፣

2.9.6. ለስፖርት እድገት በሚበጁ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ይመከራል፣ የውሳኔ ሀሳብም ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

2.9.7. የምክር ቤቱን የውስጥ መመሪያዎችን የማሻሻያ ሀሳብ ያዘጋጃል፣ ያስፀድቃል፣

2.9.8. የከተማውን አስተዳደር ዓመታዊ የውድድር ካላንደር መርምሮ ያፀድቃል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣

2.9.9. ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ የተለያዩ ጉዳዮችን መርምሮ ያቀርባል፣ አጀንዳዎችን ይቀርፃል፣ በጉባኤው በክብር እንግድነት የሚጋበዙና የሚሳተፉ አካላትን ይለያል፡፡

2.9.10. ስፖርት ምክር ቤቱን ድጋፍ የሚጠይቁ አካላት ሲቀርቡ ጉዳዩን መርምሮ ይወስናል፣

2.9.11. የስፖርት ምክር ቤት ጉባኤ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ እንዲካሄድ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል፡፡

2.9.12. በስፖርት ምክር ቤቱ የሚጸድቁ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ በስራ አስፈፃሚ በማስፀደቅ በቀጣይ በምክር ቤቱ ጉባኤ እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

2.9.13. አስፈላጊ የሆኑ ንዑስን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ይከታተላል፣ ወደ ተግባር እንዲገቡም ያደርጋል፡፡

2.9.14. የተለያዩ የሀብት ማሰባሰቢያ መንገዶችን ቀይሶ ይሰራል እንደ አስፈላጊነቱ ስራ አስፈጻሚ አካላት ካመነበት ሀብት ከተለያዩ አካላት ጋር በስምምነት /በኮሚሽን /ሀብት የማሰባሰብ ስራዎችን ይሰራል ተግባር ላይ እንዲዉል ያደርጋል፡፡

## 2.10. የምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስብሰባ ስነ-ስርዓት

2.10.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ በየወሩ ይደረጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊያደረግ ይቻላል፣

2.10.2. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ ወቅት ከግማሽ በላይ የሆኑ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፣

2.10.3. ምልዓተ ጉባዔ ሳይሟላ ቀርቶ በቀጣይ በሚጠራ አስቸኳይ ስብሰባ በተገኙ አባላት ውሳኔ ማሳለፍ ይቻላል፡፡

2.10.4. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ በተለያየ ምክንያት በዕለቱ ስብሰባ ላይ ካልተገኙ የኮሚቴው ም/ሰብሳቢ የዕለቱን ስብሰባ ይመራሉ፣

2.10.5. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ውሳኔ የሚፀድቀው በድምፅ ብልጫ በግልጽ ድምፅ አሰጣጥ ዘዴ ነው፣

2.10.6. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ ወቅት በአንድ ጉዳይ ላይ ድምፅ እኩል ከሆነ ሰባሳቢው የሚደግፈው ወገን አሸናፊ ይሆናል፡፡

## 2.11. የምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስራ ዘመን

2.11.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን አራት ዓመት ነው፣

2.11.2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ዝርዝር የሚፀድቀው በስፖርት ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ነው፣

2.11.3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፣

## 2.12. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

2.12.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎችን በሰብሳቢነት ይመራል፣

2.12.2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን የስብሰባ አጀንዳዎች ከፀሐፊው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣

2.12.3. የቢሮ የክፍያና ሒሳብ ኃላፊ ጋር በመሆን የምክር ቤቱን ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፣

2.12.4. የስራ አስፈፃሚውን ተግባራት በበላይነት ይመራል፣

2.12.5. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ወቅት ድምጽ እኩል ከተከፈለ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

### 2.13. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

2.13.1. ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሰራል፣

### 2.14. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሐፊ ስልጣንና ተግባር

2.14.1. ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ጋር በመሆን የስብሰባ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፣

2.14.2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስብሰባ ቃለ-ጉባኤዎችን ልዩ ልዩ ሰነዶችን በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፣

2.14.3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፣

2.14.4. አስፈላጊ ሰነዶችንም ለአባላቱ ያሰራጫል፡

# ክፍል ሦስት

## 3. የክ/ከተማ ስፖርት ምክር ቤት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር

### 3.1. የክ/ከተማው ስፖርት ምክር ቤት አወቃቀር

3.1.1. ጠቅላላ ጉባኤ

3.1.2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

3.1.3. ኦዲት ኮሚሽን ናቸው

### 3.2. የክ/ከተማው ስፖርት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ አባላት

3.2.1. **በድምፅ የሚሳተፉ የስፖርት ም/ቤቱ ጉባኤ አባላት**

3.2.1.1. የክ/ከተማው ዋና ስራ አስፈፃሚ ------------------------------------------ ሰብሳቢ

3.2.1.2. የክ/ከተማው ወጣቶችና ስፖርት ፅ/ቤት ኃላፊ ---------------------------- ም/ሰብሳቢ

3.2.1.3. የስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ቡድን መሪ -------------------- ፀሐፊ

3.2.1.4. የክ/ከተማው የስራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ፅ/ቤት ኃላፊ ------- አባል

3.2.1.5. የክ/ከተማው ፐብሊክ ሰርቭስና የሰዉ ሀብት ልማት ፅ/ቤት ኃላፊ ------ አባል

3.2.1.6. የክ/ከተማው ፋይናንስ ፅ/ቤት ኃላፊ ---------------------------------------- አባል

3.2.1.7. የክ/ከተማው ሰላምና ጸጥታ ፅ/ቤት ኃላፊ -------------------------------- አባል

3.2.1.8. የክ/ከተማው መሬት ልማትና አስተዳደር ፅ/ቤት ኃላፊ ----------------- አባል

3.2.1.9. የክ/ከተማው ንግድ ፅ/ቤት ኃላፊ ------------------------------------------ አባል

3.2.1.10. የክ/ከተማው ጤና ቢሮ ኃላፊ -------------------------------------------- አባል

3.2.1.11. የክ/ከተማው ትምህርት ፅ/ቤት ኃላፊ ------------------------------------ አባል

3.2.1.12. የክ/ከተማው ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ፅ/ቤት ኃላፊ --------- አባል

3.2.1.13. የክ/ከተማው ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ፅ/ቤት ኃላፊ --------------- አባል

3.2.1.14. የክ/ከተማው ኮሚኒኬሽን ፅ/ቤት ኃላፊ ----------------------------------- አባል

3.2.1.15. የክ/ከተማው ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ --------------------------------------- አባል

3.2.1.16. የክ/ከተማው ግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ፅ/ቤት ኃላፊ ------------------- አባል

3.2.1.17. በክፍለ ከተማው የሚገኙ ወረዳዎች ስፖርት ም/ቤት ሰብሳቢዎች ---- አባል

3.2.1.18. በክ/ከተማው የሚገኝ ታዋቂ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት -------------------- አባል

3.2.1.19. በክ/ከተማው የስፖርት ማህበራት ፕሬዝዳንቶች ------------------------ አባል

3.2.1.20. የክ/ከተማው አካል ጉዳተኞች ማህበር ሊቀመንበር --------------------- አባል

3.2.1.21. የክ/ከተማው መምህራን ማህበር ሊቀመንበር ---------------------------- አባል

3.2.1.22. የክ/ከተማው ንግድ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ----------------------------- አባል

3.2.1.23. የክ/ከተማው ሰራተኞች ማህበር ሊቀመንበር ---------------------------- አባል

3.2.1.24. የክ/ከተማው ወጣቶች ፌዴሬሽን ሰብሳቢ --------------------------------- አባል

3.2.1.25. የክ/ከተማው ሴቶች ፌዴሬሽን ሰብሳቢ------------------------------------ አባል

3.2.1.26. የክ/ከተማው እድሮች ም/ቤት ሰብሳቢ------------------------------------- አባል

3.2.1.27. የክ/ከተማው ክፍያና ሒሳብ ቡድን አስተባባሪ --------------------------- አባል

3.2.1.28. የስፖርት ትምህርትና ስልጠና ቡድን አስተባባሪ ------------------------ አባል

3.2.1.29. የማህበረሰብ ስፖርት ማስፋፊያና ተሳትፎ ቡድን አስተባባሪ ---------- አባል

3.2.1.30. የማዕከላትና ማዘውተሪያ ስፍራዎች ልማትና አስተዳደር ቡድን መሪ ------ አባል

3.2.2. **ያለድምጽ የሚሳተፉ የጉባኤ አባላት**

3.2.2.1. በክ/ከተማው በፑል ደረጃ ያሉ ደጋፊ ቡድኖች፣

3.2.2.2. የወረዳ ወጣቶችና ስፖርት ፅ/ቤት ኃላፊዎች፣

3.2.2.3. የወረዳ የስ/ማ/ማ/ስ/ውድድር ቡድን አስተባበሪዎች፣

3.2.2.4. የክ/ከተማው ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ባለሙያዎች

3.2.2.5. የአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ተወካይ፣

3.2.2.6. የአ/አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክተር፣

3.2.2.7. የክ/ከተማው የህትመትና ኤሌክትሮኒክስ የሚዲያ ተቋማት ተወካዮች፣

3.2.2.8. የክ/ከተማው ወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ስራ አስኪያጆች፣

3.2.2.9. የሙያ ማህበራት

3.2.2.10. በክ/ከተማው ለስፖርት እንቅስቃሴ የላቀ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ 3 ድርጅቶች

3.2.2.11. **ለስፖርት እንቅስቃሴ የላቀ አስተዋጽኦ ያደረጉ 3 ታዋቂ ግለሰቦች ---------- አባል**

3.2.2.12. የአካል ጉዳተኞችና መስማት የተሳናቸዉ ማሀበራት

### 3.3. የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባዓ ስልጣንና ተግባር

3.3.1. የክ/ከተማ አስተዳደሩን ስፖርት በበላይነት ይመራል፣

3.3.2. የምክር ቤቱን ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቋቁማል፣ አባላቱንም ይሰይማል፣ አባላቱ ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ ውሳኔ ይሰጣል፣

3.3.3. የወረዳ ስፖርት ም/ቤቶች እንዲቋቋሙ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

3.3.4. በስሩ አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ተግባር ይሰጣል፣

3.3.5. ልዩ ልዩ የውስጥ መመሪያዎችን ያወጣል፣ በስራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፣

3.3.6. ለስፖርት ምክር ቤቱ የኦዲት ኮሚሽን ይሰይማል፣

3.3.7. ለስፖርት ዕድገት መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ የበላይ አካል ውሳኔ የሚጠይቁ ጉዳዮችን አጥንቶ ለክ/ከተማው የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣

3.3.8. በመኖሪያ አካባቢ፣ በትምህርት ተቋማትና በመስሪያ ቤቶች የሚካሄደውን የክ/ከተማ አስተዳደር ስፖርት እንቅስቃሴን እየገመገመና እያጠና የሚዳብርበትን ሁኔታ ይቀይሳል፣

3.3.9. በሀገር ዓቀፍና በከተማ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶት በክ/ከተማችን እየተተገበረ ያለውን የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ልማት ስልጠና ፕሮግራምን ለማሳደግ ይሰራል፣

3.3.10. የክ/ከተማው ነዋሪዎች በስፖርት ለሁሉምና ባህላዊ ስፖርቶች እንዲሳተፉ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣

3.3.11. አካል ጉዳተኞችና ሴቶች በስፖርት እንዲሳተፉ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

3.3.12. የክ/ከተማው ባለሃብት በስፖርት ዘርፍ ኢንቨስት እንዲያደርጉ፣ በማዘውተሪያ ስፍራዎች ግንባታ፣ በስፖርት ማበልፀጊያ ተቋማት ምስረታና በስፖርት ትጥቅና መሳርያዎች የማምረት ተግባር ላይ እንዲሰማሩ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

3.3.13. የህብረተሰቡ የስፖርት ግንዛቤ እንዲዳብር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፣

3.3.14. የስፖርት ጥናትና ምርምር ስራዎች እንዲበረታቱ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

3.3.15. በክ/ከተማው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲስፋፉ፣ እንዲጠበቁና እንዲገነቡ ተገቢውን ይፈፅማል፣

3.3.16. ለስፖርቱ መስፋፋት የሚረዱ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

3.3.17. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠቃለው የሚቀርቡትን የክ/ከተማ አስተዳደሩን የስፖርት ዓመታዊ የስራ እቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል፣

3.3.18. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠቃለው የሚቀርቡለትን የአስተዳደሩን ስፖርት የስራ ክንውንና የፋይናንስ ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፣

3.3.19. በስፖርት ዙሪያ የሚነሱ ችግሮችን መርምሮ መፍትሄ ይሰጣል፣

3.3.20. የም/ቤቱንና የፌዴሬሽኖችን የፋይናንስ መመሪያን ያወጣል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

3.3.21. በገቢ ምንጮቹ አማካይነት የተገኘውን ገንዘብና ንብረት ያስተዳድራል፣

### 3.4. የስፖርት ም/ቤት ስብሰባ ስነ-ስርዓት

3.4.1. ምክር ቤቱ በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፣

3.4.2. የም/ቤቱ የስብሰባ ቀንና ቦታ መግለጫ፣ ያለፈው ቃለ-ጉባኤና የመወያያ አጀንዳዎች ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር ከስብሰባው ሶስት ቀን በፊት ለአባላቱ ይደርሳል፣

3.4.3. በምክር ቤቱ ስብሰባ ወቅት ከግማሽ በላይ የሆኑ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው ይሆናል፣

3.4.4. አጠቃላይ ውሳኔን የሚጠይቁ ጉዳዩች ማለትም የውስጥ መመሪያዎችን ማፅደቅ፣ ዕቅድና በጀት ማፅደቅ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ ጉዳዮች በሚቀርብበት ጊዜ ቢያንስ $50^{+1}$ አባላት መገኘት አለባቸው፣

3.4.5. የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የሚፀድቀው በድምጽ ብልጫ ሆኖ ለሁሉም ግልጽ በሆነ የድምጽ አሰጣጥ መንገድ ነው፣

3.4.6. በአንድ ጉዳይ ላይ በሚሰጥር ድምጽ አሰጣጥ የተሰጠው ድምጽ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው አሸናፊ ይሆናል፣

### 3.5. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

3.5.1. በማንኛውም ስፍራ የምክር ቤቱ ህጋዊ ተጠሪ ነው፣

3.5.2. የምክር ቤቱን ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ይመራል፣

3.5.3. በምክር ቤቱ ስብሰባ ወቅት ድምጽ እኩል ከተከፈለ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣

3.5.4. የምክር ቤቱን ስብሰባ አጀንዳዎች ከፀሐፊው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣

3.5.5. የምክር ቤቱ ዕቅድና በጀት እንዲሁም የዕቅድ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርት መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣

3.5.6. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣

3.5.7. የምክር ቤቱን ጠቅላላ ስራዎች ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

### 3.6. የምክር ቤቱ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

3.6.1. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሰራል፤

3.6.2. ከም/ቤቱ ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፤

### 3.7. የምክር ቤቱ ፀሐፊ ስልጣንና ተግባር

3.7.1. ከምክር ቤቱ ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢ ጋር በመሆን የስብሰባ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፣

3.7.2. የምክር ቤቱን ዕቅድና በጀት እንዲሁም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ያዘጋጃል፣

3.7.3. የምክር ቤቱ ስብሰባዎች ቃለ-ጉባኤ እንዲያዝ ያደርጋል፣

3.7.4. የምክር ቤቱ ልዩ ልዩ ሰነዶች በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፣

3.7.5. በምክር ቤቱ ሰብሳቢ በሚሰጠው ውክልና መሰረት የጽሁፍ ልውውጦችን ያደርጋል፣

3.7.6. ለምክር ቤቱ አባላትና ለሚመለከታቸው አካላት የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፣ አስፈላጊ ሰነዶችንም ለአባላቱ ያሰራጫል፣

3.7.7. የምክር ቤቱን መሰብሰቢያ አዳራሽ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ አስፈላጊ ሁኔታዎችም መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣

## 3.8. የክ/ከተማ ስፖርት ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

3.8.1. የክ/ከተማው ወጣቶችና ስፖርት ፅ/ቤት ኃላፊ ---------------------------- ሰብሳቢ

3.8.2. የክ/ከ/ወጣ/ስፖ/ፅ/ቤት/ስፖ/ማህ/ማደ/ውድድር ቡድን አስተባባሪ---------- ም/ሰብሳቢ

3.8.3. የክ/ከ/ወጣ/ስፖ/ፅ/ቤት ማህበራት ማደራጃ ባለሙያ ----------------------- ፀሐፊ

3.8.4. የክ/ከተማው ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ----------------------------------------- አባል

3.8.5. የክ/ከተማው ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ ------------------------------------ አባል

3.8.6. የክ/ከተማው ንግድ ቢሮ ኃላፊ --------------------------------------------- አባል

3.8.7. የክ/ከተማው ጤና ቢሮ ኃላፊ ---------------------------------------------- አባል

3.8.8. የክ/ከተማው ትምህርት ቢሮ ኃላፊ --------------------------------------- አባል

3.8.9. የክ/ከተማው ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ------------ አባል

3.8.10. የክ/ከተማው ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ --------------- አባል

3.8.11. የክ/ከተማው ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የክፍያና ሒሳብ ዳይሬክተር - አባል

3.8.12. የክ/ከተማው ግ/ን/አስተዳደር ዳይሬክተር ------------------------------ አባል

3.8.13. የ2 ስፖርት ማህበራት ፕሬዝዳንቶች ----------------------------------- አባል

3.8.14. የክ/ከተማው ክፍያና ሒሳብ ቡድን አስተባባሪ ------------------------ አባል

3.8.15. የክ/ከተማው ስፖርት ትምህርትና ስልጠና ቡድን አስተባባሪ -------- አባል

3.8.16. የክ/ከተማው ማህበ/ስፖርት ማስፋፊያና ተሳትፎ ቡድን አስተባባሪ - አባል

3.8.17. የክ/ከተማው ማዕከ/ማዘው/ስፍራዎች ልማትና አስተዳደር ቡድን መሪ ---- አባል

## 3.9. የምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

3.9.1. በምክር ቤቱ የሚወጡ መመሪያዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣

3.9.2. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣

3.9.3. በስፖርት ጽ/ቤት አማካይነት ተዘጋጅተው የሚቀርቡትን ዓመታዊ እቅድና በጀት እንዲሁም የእቅድ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት መርምሮ ለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ሲፀድቅም በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣

3.9.4. ከስፖርት ም/ቤቱ በጀት በዝውውር ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራት ከስፖርት ማህበራትና ከጽ/ቤቱ ሲቀርብ መርምሮ እንዲዘዋወር ያደርጋል፡

3.9.5. ከጽ/ቤቱና ከስፖርት ማህራት ጋር በመሆን ክ/ከተማ አቀፍና ከተማ አቀፍ የስፖርት ውድድሮችንና ፌስቲቫሎችን ያዘጋጃል፣

3.9.6. ለስፖርት እድገት በሚበጁ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ይመከራል፣ የውሳኔ ሀሳብም ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

3.9.7. የምክር ቤቱን የውስጥ መመሪያዎችን የማሻሻያ ሀሳብ ያዘጋጃል፣ ያስጸድቃል፣

3.9.8. የክ/ከተማውን አስተዳደር ዓመታዊ የውድድር ካላንደር መርምሮ ያጸድቃል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣

3.9.9. ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ የተለያዩ ጉዳዮችን መርምሮ ያቀርባል፣

3.9.10. ስፖርት ምክር ቤቱን ድጋፍ የሚጠይቁ አካላት ሲቀርቡ ጉዳዩን መርምሮ ይወስናል፣

3.9.11. አስፈላጊ የሆኑ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ይከታተላል፡፡

3.9.12. የተለያዩ የሀብት ማሰባሰቢያ መንገዶችን ቀይሶ ይሰራል እንደ አስፈላጊነቱ ስራ አስፈጻሚ አካላት ካመነበት ሀብት ከተለያዩ አካላት ጋር በስምምነት /በኮሚሽን /ሀብት የማሰባሰብ ስራዎችን ይሰራል ተግባር ላይ እንዲዉል ያደርጋል፡፡

### 3.10. የምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስብሰባ ስነ-ስርዓት

3.10.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ በየወሩ ይደረጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊያደረግ ይቻላል፤

3.10.2. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ ወቅት ከግማሽ በላይ የሆኑ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

3.10.3. ምልዓተ ጉባዔ ሳይሟላ ቀርቶ በቀጣይ በሚጠራ አስቸኳይ ስብሰባ በተገኙ አባላት ውሳኔ ማሳለፍ ይቻላል፡፡

3.10.4. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ በተለያየ ምክንያት በዕለቱ ስብሰባ ላይ ካልተገኙ የኮሚቴው ም/ሰብሳቢ የዕለቱን ስብሰባ ይመራሉ

3.10.5. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ውሳኔ የሚጸድቀው በድምጽ ብልጫ በግልጽ ድምጽ አሰጣጥ ዘዴ ነው

3.10.6. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ ወቅት በአንድ ጉዳይ ላይ ድምጽ እኩል ከሆነ ሰባሳቢው የሚደግፈው ወገን አሸናፊ ይሆናል፡፡

### 3.11. የምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስራ ዘመን

3.11.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን አራት ዓመት ነው፣

3.11.2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ዝርዝር የሚፀድቀው በስፖርት ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ነው፣

3.11.3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ከወከላቸው አካል የውክልና ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው፤

3.11.4. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፣

### 3.12. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

3.12.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎችን በሰብሳቢነት ይመራል፣

3.12.2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን የስብሰባ አጀንዳዎች ከፀሐፊው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣

3.12.3. ከፋይናንስ ቡድን መሪ ጋር በመሆን የምክር ቤቱን ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፣

3.12.4. የስራ አስፈፃሚውን ተግባራት በበላይነት ይመራል፣

3.12.5. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ወቅት ድምጽ እኩል ከተከፈለ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣

### 3.13. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

3.13.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሰራል፣

3.13.2. ከክፍያና ሂሳብ ቡድን መሪ ጋር በመሆን የምክር ቤቱን ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፣

### 3.14. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሐፊ ስልጣንና ተግባር

3.14.1. ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ጋር በመሆን የስብሰባ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፣

3.14.2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስብሰባ ቃለ-ጉባኤዎችን ልዩ ልዩ ሰነዶችን በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፣

3.14.3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፣

3.14.4. አስፈላጊ ሰነዶችንም ለአባላቱ ያሰራጫል፣

# ክፍል አራት

## 4. የክ/ከተማ ስፖርት ምክር ቤት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር

### 4.1. የወረዳው ስፖርት ምክር ቤት አወቃቀር

4.1.1. ጠቅላላ ጉባኤ

4.1.2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

4.1.3. ኦዲት ኮሚሽን ናቸው

### 4.2. የወረዳው ስፖርት ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባኤ አባላት

4.2.1. **በድምፅ የሚሳተፉ የስፖርት ም/ቤቱ ጉባኤ አባላት**

4.2.1.1. የወረዳው ዋና ስራ አስፈፃሚ ------------------------------------------------ ሰብሳቢ

4.2.1.2. የወረዳው ወጣቶችና ስፖርት ፅ/ቤት ኃላፊ ------------------------------- ም/ሰብሳቢ

4.2.1.3. የወረዳው ስፖ/ማህ/ማደራጃ፣ ስልጠናና ውድድር ቡድን አስተባባሪ --- ፀሐፊ

4.2.1.4. የወረዳው የስራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ፅ/ቤት ኃላፊ --- አባል

4.2.1.5. የወረዳው ፐብሊክ ሰርቨስና የሰዉ ሀብት ልማት ፅ/ቤት ኃላፊ --------- አባል

4.2.1.6. የወረዳው ፋይናንስ ፅ/ቤት ኃላፊ -------------------------------------------- አባል

4.2.1.7. የወረዳው ሰላምና ጸጥታ ፅ/ቤት ኃላፊ ------------------------------------ አባል

4.2.1.8. የወረዳው መሬት ልማትና አስተዳደር ፅ/ቤት ኃላፊ --------------------- አባል

4.2.1.9. የወረዳው ንግድ ፅ/ቤት ኃላፊ ---------------------------------------------- አባል

4.2.1.10. የወረዳው ጤና ቢሮ ኃላፊ ------------------------------------------------ አባል

4.2.1.11. የወረዳው ትምህርት ፅ/ቤት ኃላፊ --------------------------------------- አባል

4.2.1.12. የወረዳው ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ፅ/ቤት ኃላፊ ------------ አባል

4.2.1.13. የወረዳው ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ፅ/ቤት ኃላፊ ------------------- አባል

4.2.1.14. የወረዳው ኮሚኒኬሽን ፅ/ቤት ኃላፊ ------------------------------------- አባል

4.2.1.15. የወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ኃላፊ -------------------------------------------- አባል

4.2.1.16. የወረዳው ግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ፅ/ቤት ኃላፊ ---------------------- አባል

4.2.1.17. በወረዳው የስፖርት ማህበራት ፕሬዝዳንቶች --------------------------- አባል

4.2.1.18. የወረዳው አካል ጉዳተኞች ማህበር ሊቀመንበር ------------------------ አባል

4.2.1.19. የወረዳው መምህራን ማህበር ሊቀመንበር ------------------------------ አባል

4.2.1.20. የወረዳው ንግድ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት -------------------------------- አባል

4.2.1.21. የወረዳው ሰራተኞች ማህበር ሊቀመንበር -------------------------------- አባል

4.2.1.22. የወረዳው ወጣቶች ፌዴሬሽን ሰብሳቢ ---------------------------------- አባል

4.2.1.23. የወረዳው ሴቶች ፌዴሬሽን ሰብሳቢ------------------------------------- አባል

4.2.1.24. የወረዳው እድሮች ም/ቤት ሰብሳቢ-------------------------------------- አባል

4.2.1.25. የወረዳው ሽማቾች ህ/ስ/ማህበር ሰብሳቢ---------------------------------- አባል

4.2.1.26. የወረዳው ክፍያና ሒሳብ ቡድን አስተባባሪ ---------------------------- አባል

4.2.1.27. የወረዳው ስፖርት ተሳትፎ፣ አካል ብቃትና ፋሲሊቲ ቡድን አስተባባሪ --- አባል

የሚያደርጉ 2 መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ----------------------- አባል

4.2.2. **ያለድምጽ የሚሳተፉ የጉባኤ አባላት**

4.2.2.1. በወረዳው በፑል ደረጃ ያሉ ደጋፊ ቡድኖች፣

4.2.2.2. የወረዳው ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት ባለሙያዎች

4.2.2.3. የክ/ከተማው ወጣቶችና ስፖርት ፅ/ቤት ተወካይ

4.2.2.4. የክ/ከተማው የስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ቡድን አስተባባሪ

4.2.2.5. የወረዳው የህትመትና ኤሌክትሮኒክስ የሚዲያ ተቋማት ተወካዮች

4.2.2.6. የወረዳው ወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከል ስራ አስኪያጅ

4.2.2.7. ሙያ ማህበራት

4.2.2.8. በወረዳው ለስፖርት እንቅስቃሴ የላቀ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ 2 ድርጅቶች

4.2.2.9. ለስፖርት እንቅስቃሴ የላቀ አስተዋጽኦ ያደረጉ 2 ታዋቂ ግለሰቦች

**4.3. የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባዔ ስልጣንና ተግባር**

4.3.1. የወረዳው አስተዳደር ስፖርት በበላይነት ይመራል፤

4.3.2. የምክር ቤቱን ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቋቁማል፣ አባላቱንም ይሰይማል፣ አባላቱ ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ ውሳኔ ይሰጣል፤

4.3.3. በስሩ አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ልዩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ተግባር ይሰጣል፤

4.3.4. ልዩ ልዩ የውስጥ መመሪያዎችን ያወጣል፣ በስራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

4.3.5. ለስፖርት ምክር ቤቱ የኦዲት ኮሚሽን ይሰይማል፤

4.3.6. ለስፖርት ዕድገት መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ የበላይ አካል ውሳኔ የሚጠይቁ ጉዳዮችን አጥንቶ ለክ/ከተማው አስተዳደር የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤

4.3.7. በመኖሪያ አካባቢ፣ በትምህርት ተቋማትና በመስሪያ ቤቶች የሚካሄደውን የወረዳው አስተዳደር ስፖርት እንቅስቃሴን እየገመገመና እያጠና የሚዳብርበትን ሁኔታ ይቀይሳል፤

4.3.8. በከተማና በክ/ከተማ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶት በወረዳው እየተተገበረ ያለውን የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ልማት ስልጠና ፕሮግራምን ለማሳደግ ይሰራል፤

4.3.9. የወረዳው ነዋሪዎች በስፖርት ለሁሉምና ባህላዊ ስፖርቶች እንዲሳተፉ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤

4.3.10. አካል ጉዳተኞችና ሴቶች በስፖርት እንዲሳተፉ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

4.3.11. የወረዳው ባለሃብት በስፖርት ዘርፍ ኢንቨስት እንዲያደርጉ፣ በማዘውተርያ ስፍራዎች ግንባታ፣ በስፖርት ማበልፀጊያ ተቋማት ምስረታና በስፖርት ትጥቅና መሳርያዎች የማምረት ተግባር ላይ እንዲሰማሩ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

4.3.12. የህብረተሰቡ የስፖርት ግንዛቤ እንዲዳብር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፣

4.3.13. የስፖርት ጥናትና ምርምር ስራዎች እንዲበረታቱ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

4.3.14. በወረዳ አስተዳደሩ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲስፋፉ፣ እንዲጠበቁና እንዲገነቡ ተገቢውን ይፈፅማል፣

4.3.15. ለስፖርቱ መስፋፋት የሚረዱ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

4.3.16. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠቃለው የሚቀርቡትን የወረዳ አስተዳደሩን የስፖርት ዓመታዊ የስራ እቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል፤

4.3.17. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠቃለው የሚቀርቡለትን የአስተዳደሩን ስፖርት የስራ ክንውንና የፋይናንስ ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፣

4.3.18. በስፖርት ዙሪያ የሚነሱ ችግሮችን መርምሮ መፍትሄ ይሰጣል፣

4.3.19. የም/ቤቱንና የኮሚቴዎችን የፋይናንስ መመሪያን ያወጣል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

4.3.20. በገቢ ምንጮቹ አማካይነት የተገኘውን ገንዘብና ንብረት ያስተዳድራል፣

### 4.4. የስፖርት ም/ቤት ስብሰባ ስነ-ስርዓት

4.4.1. ምክር ቤቱ በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፣

4.4.2. የም/ቤቱ የስብሰባ ቀንና ቦታ መግለጫ፣ ያለፈው ቃለ-ጉባኤና የመወያያ አጀንዳዎች ከአስፈላጊ ሰነዶች ጋር ከስብሰባው ሶስት ቀን በፊት ለአባላቱ ይደርሳል፣

4.4.3. በምክር ቤቱ ስብሰባ ወቅት በድምፅ ከሚሳተፉት ከግማሽ በላይ የሆኑ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው ይሆናል፣

4.4.4. አጠቃላይ ውሳኔን የሚጠይቁ ጉዳዩች ማለትም የውስጥ መመሪያዎችን ማፅደቅ፣ ዕቅድና በጀት ማፅደቅ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ ጉዳዮች በሚቀርብበት ጊዜ ቢያንስ 50+1 አባላት መገኘት አለባቸው፣

4.4.5. የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የሚፀድቀው በድምፅ ብልጫ ሆኖ ለሁሉም ግልፅ በሆነ የድምጽ አሰጣጥ መንገድ ነው፣

4.4.6. በአንድ ጉዳይ ላይ በሚሰጥር ድምጽ አሰጣጥ የተሰጠው ድምፅ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው አሸናፊ ይሆናል፣

**4.5. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር**

4.5.1. በማንኛውም ስፍራ የምክር ቤቱ ህጋዊ ተጠሪ ነው፣

4.5.2. የምክር ቤቱን ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ይመራል፣

4.5.3. በምክር ቤቱ ስብሰባ ወቅት ድምጽ እኩል ከተከፈለ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፣

4.5.4. የምክር ቤቱን ስብሰባ አጀንዳዎች ከፀሐፊው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣

4.5.5. የምክር ቤቱ ዕቅድና በጀት እንዲሁም የዕቅድ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርት መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣

4.5.6. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣

4.5.7. የምክር ቤቱን ጠቅላላ ስራዎች ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

**4.6. የምክር ቤቱ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር**

4.6.1. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሰራል፤

4.6.2. ከም/ቤቱ ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፤

**4.7. የምክር ቤቱ ፀሐፊ ስልጣንና ተግባር**

4.7.1. ከምክር ቤቱ ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢ ጋር በመሆን የስብሰባ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፤

4.7.2. የምክር ቤቱን ዕቅድና በጀት እንዲሁም የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ያዘጋጃል፤

4.7.3. የምክር ቤቱ ስብሰባዎች ቃለ-ጉባኤ እንዲያዝ ያደርጋል፤

4.7.4. የምክር ቤቱ ልዩ ልዩ ሰነዶች በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፤

4.7.5. በምክር ቤቱ ሰብሳቢ በሚሰጠው ውክልና መሰረት የጽሁፍ ልውውጦችን ያደርጋል፤

4.7.6. ለምክር ቤቱ አባላትና ለሚመለከታቸው አካላት የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፣ አስፈላጊ ሰነዶችንም ለአባላቱ ያሰራጫል፣

4.7.7. የምክር ቤቱን መሰብሰቢያ አዳራሽ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ አስፈላጊ ሁኔታዎችም መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣

## 4.8. የወረዳው ስፖርት ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

4.8.1. የወረዳው ወጣቶችና ስፖርት ፅ/ቤት ኃላፊ -------------------------------- ሰብሳቢ

4.8.2. የወረዳው ስፖ/ማህ/ማደራጃ፣ ስልጠናና ውድድር ቡድን አስተባባሪ ----- ም/ሰብሳቢ

4.8.3. የወረዳው ስፖ/ማህ/ማደራጃ፣ ስልጠናና ውድድር ባለሙያ -------------- ፀሐፊ

4.8.4. የወረዳው ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ------------------------------------------ አባል

4.8.5. የወረዳው ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ -------------------------------------- አባል

4.8.6. የወረዳው ንግድ ቢሮ ኃላፊ ---------------------------------------------- አባል

4.8.7. የወረዳው ጤና ቢሮ ኃላፊ ------------------------------------------------ አባል

4.8.8. የወረዳውትምህርት ቢሮ ኃላፊ ---------------------------------------------- አባል

4.8.9. የወረዳው ሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ----------------- አባል

4.8.10. የወረዳው ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ---------------------- አባል

4.8.11. የወረዳው የክፍያና ሒሳብ ቡድን መሪ ----------------------------------- አባል

4.8.12. የክ/ከተማው ግ/ን/አስተዳደር ቡድን መሪ --------------------------------- አባል

4.8.13. የ1 ስፖርት ማህበራት ፕሬዝዳንቶች ------------------------------------- አባል

4.8.14. የወረዳው ስፖርት ተሳትፎ፣ አካል ብቃትና ፋሲሊቲ ቡድን አስተባባሪ ------ አባል

4.8.14.1. የአካል ጉዳተኞችና መስማት የተሳናቸዉ ማህበራት

## 4.9. የምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

4.9.1. በምክር ቤቱ የሚወጡ መመሪያዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣

4.9.2. የምክር ቤቱ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣

4.9.3. በወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት አማካይነት ተዘጋጅተው የሚቀርቡትን ዓመታዊ እቅድና በጀት እንዲሁም የእቅድ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት መርምሮ ለምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ሲፀድቅም በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣

4.9.4. ከስፖርት ም/ቤቱ በጀት በዝውውር ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራት ከስፖርት ማህበራትና ከጽ/ቤቱ ሲቀርብ መርምሮ እንዲዘዋወር ያደርጋል፣

4.9.5. ጽ/ቤቱና ከስፖርት ማህራት ጋር በመሆን ወረዳ አቀፍ የስፖርት ውድድሮችንና ፌስቲቫሎችን ያዘጋጃል፣ እንዲያስተናግድ እድል ከተሰጠው ያስተናግዳል፣

4.9.6. ለስፖርት እድገት በሚበጁ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ይመከራል፣ የውሳኔ ሀሳብም ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

4.9.7. የምክር ቤቱን የውስጥ መመሪያዎችን የማሻሻያ ሀሳብ ያዘጋጃል፣ ያስጸድቃል፣

4.9.8. የወረዳውን አስተዳደር ዓመታዊ የውድድር ካላንደር መርምሮ ያጸድቃል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣

4.9.9. ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ የተለያዩ ጉዳዮችን መርምሮ ያቀርባል፣

4.9.10. ስፖርት ምክር ቤቱን ድጋፍ የሚጠይቁ አካላት ሲቀርቡ ጉዳዩን መርምሮ ይወስናል፣

4.9.11. አስፈላጊ የሆኑ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ይከታተላል፣

**4.10. የምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስብሰባ ስነ-ስርዓት**

4.10.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ በየወሩ ይደረጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊያደረግ ይቻላል፣

4.10.2. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ ወቅት ከግማሽ በላይ የሆኑ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፣

4.10.3. ምልዓተ ጉባዔ ሳይሟላ ቀርቶ በቀጣይ በሚጠራ አስቸኳይ ስብሰባ በተገኙ አባላት ውሳኔ ማሳለፍ ይቻላል፣

4.10.4. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ በተለያየ ምክንያት በዕለቱ ስብሰባ ላይ ካልተገኙ የኮሚቴው ም/ሰብሳቢ የዕለቱን ስብሰባ ይመራሉ፣

4.10.5. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ውሳኔ የሚጸድቀው በድምጽ ብልጫ በግልጽ ድምጽ አሰጣጥ ዘዴ ነው፣

4.10.6. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ ወቅት በአንድ ጉዳይ ላይ ድምፅ እኩል ከሆነ ሰባሳቢው የሚደግፈው ወገን አሸናፊ ይሆናል፡፡

4.10.7. የተለያዩ የሀብት ማሰባሰቢያ መንገዶችን ቀይሶ ይሰራል እንደ አስፈላጊነቱ ስራ አስፈጻሚ አካላት ካመነበት ሀብት ከተለያዩ አካላት ጋር በስምምነት /በኮሚሽን /ሀብት የማሰባሰብ ስራዎችን ይሰራል ተግባር ላይ እንዲዉል ያደርጋል፡፡

**4.11. የምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስራ ዘመን**

4.11.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን አራት ዓመት ነው፣

4.11.2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ዝርዝር የሚፀድቀው በስፖርት ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ነው፣

4.11.3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ከወከላቸው አካል የውክልና ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው፣

4.11.4. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፣

**4.12. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር**

4.12.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎችን በሰብሳቢነት ይመራል፣

4.12.2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን የስብሰባ አጀንዳዎች ከፀሐፊው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣

4.12.3. ከፋይናንስ ቡድን መሪ ጋር በመሆን የምክር ቤቱን ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፣

4.12.4. የስራ አስፈፃሚውን ተግባራት በበላይነት ይመራል፣

4.12.5. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ወቅት ድምጽ እኩል ከተከፈለ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣

### 4.13. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

4.13.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሰራል፣

4.13.2. ከፋይናንስ ቡድን መሪ ጋር በመሆን የምክር ቤቱን ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፣

### 4.14. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሐፊ ስልጣንና ተግባር

4.14.1. ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ጋር በመሆን የስብሰባ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፤

4.14.2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስብሰባ ቃለ-ጉባኤዎችን ልዩ ልዩ ሰነዶችን በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፣

4.14.3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፣

4.14.4. አስፈላጊ ሰነዶችንም ለአባላቱ ያሰራጫል፣

# ክፍል አምስት

## 5. የኦዲት ኮሚሽንና የምክር ቤቱ በጀት አፈፃፀም

### 5.1. የኦዲት ኮሚሽን

5.1.1. የኦዲት ኮሚሽን አባላት ብዛት ሶስት ሲሆኑ በስፖርት ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ አባላቱ ይሰየማሉ፣

5.1.2. 3ቱን የኦዲት ኮሚሽን አባላት በም/ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት አማካኝነት ተለይተው ለጠ/ጉባዔው በማቅረብ የማስፀደቅ ስራ ይሰራል፣

5.1.3. የኦዲት ኮሚሽኑ አንድ ሰብሳቢ፣ አንድ ፀሐፊና አንድ አባል ይኖሩታል፤

5.1.4. የኦዲት ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለስፖርት ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

5.1.4.1.የስፖርት ምክርቤቱ የፋይናንስና የንብረት አያያዝ /አወጋገድ/ ህጋዊ አሰራርን የተከተለ መሆኑን ይቆጣጠራል፣

5.1.4.2.በስፖርት ምክር ቤቱ የፀደቀው በጀት በአግባቡ በወጪና ገቢ ስርዓትን የተከተለ መሆኑን ይቆጣጠራል፣

5.1.4.3.በስፖርት ምክር ቤቱ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ወቅት የኦዲት ሪፖርት የማቅረብ፣

5.1.4.4.ስፖርት ምክር ቤቱ የወጪና የገቢ ስርኣቶች በም/ቤቱ የፋይናንስና የንብረት መመሪያ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ መሰረት የተከናወነ መሆኑን የመቆጣጠር፣

5.1.4.5.እንደ አስፈላጊነቱ ኦዲት በዉጪ ኦዲተር ይደረጋል

### 5.2. የስፖርት ምክር ቤቱ የገቢ ምንጭ

5.2.1. ከከተማ፣ ከክ/ከተማና ወረዳ አስተዳደ የሚሰጥ የበጀት ድጎማ፣

5.2.2. ከስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ኪራይ፣

5.2.3. ከስፖርት ማዕከላት የሚሰጥ ድጎማ፣

5.2.4. ከልዩ ልዩ ኪራይና ከቲሴራ ሽያጭ፣

5.2.5. ከስፖርትማህበራት ምዝገባና የፈቃድ እድሳት፣

5.2.6. ከስፖርት ውድድሮች መግቢያ ትኬት ሽያጭ፣

5.2.7. ከስፖንሰርሺፕ ገቢዎች፣

5.2.8. ከንግዱ ማህበረሰብ፣

5.2.9. ከከተማ አስተዳደሩ ነዋሪ፣

5.2.10. ከመንግስት ሰራተኞች፣

5.2.11. ከልዩ ልዩ ገቢዎች፣

## 5.3. የባንክ ሂሳብ

5.3.1. የስፖርት ም/ቤቱ በስሙ የተከፈተ የባንክ ሂሳብ ይኖረዋል፣

5.3.2. የስፖርት ም/ቤቱ ሀብት የሚሰበሰበው በስፖርት ምክር ቤቱ ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ብቻ ገቢ ይደረጋል፡፡

5.3.3. ማንኛዉ የስፖርት ማህበራት አካዉንት የቢሮ ሀላፊ ሲያረጋገጥ ብቻ እንዲከፍት ይደረጋል

## 5.4. ሂሳብ ስለማንቀሳቀስ

5.4.1. የከተማው ስፖርት ም/ቤት ሂሳብ በስፖርት ምክር ቤቱ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ወይም ም/ሰብሳቢና የክፈለ ከተማዉ ክፍያና ሂሳብ ዳይሬክቶሬት ጣምራ ፊርማ ይንቀሳቀሳል፣

5.4.2. የክ/ከተማና የወረዳ ስፖርት ም/ቤት ሂሳብ በስፖርት ምክር ቤቱ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ፣ ም/ሰብሳቢና የክፍለ ከተማ ሆነ በወረዳ ምክርቤቱ ያለበተ ፑል ፋይናስ ቡድን መሪ ጣምራ ፊርማ ይንቀሳቀሳል፣

5.4.3. በስፖርት ምክር ቤቱ ስራቸውን ለሚያስተዳድሩ ፌዴሬሽኖች ብቻ የተፈቀደ በጀት በፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ወይም ም/ፕሬዝዳንት ወይም ፅ/ቤት ኃላፊ በፋይናስ ባለሙያ በጋራ ለስራ አስፈጻሚ ቀርቦ ሲፈቀድ ወጪ ይሆናል፣

5.4.4. የከተማ፣ ክ/ከተማና ወረዳ ስፖርት ምክር ቤቱ በጀት በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም ምክትል ሰብሳቢ ቀርቦ ሲፈቀድ ብቻ ወጪ ይሆናል፣

5.4.5. ማንም ሰው በምክር ቤቱ የወጪ ማዘዣ ላይ ራሱ ጠያቂ፣ አፅዳቂ ፈቃጅና ወሳኝ ሊሆን አይችልም፣

## 5.5. የገንዘብ አሰባሰብ

5.5.1. ለስፖርት ም/ቤቱ እንቅስቃሴ በተለያየ መንገድ የሚገኝ ገንዘብ በምክር ቤቱ ከተፈቀደለት አካል በም/ቤቱ ስም በታተመ ደረሰኝ በስተቀር ማንም ገንዘብ ሊሰበሰብ አይችልም፣

5.5.2. በየትኛውም መንገድ ለስፖርት ም/ቤት የሚገኙ ልዩ ልዩ ገቢዎች በስፖርት ምክር ቤቱ አካውንት ገቢ ሳይሆኑ ወጪ መሆን አይችሉም፣

## 5.6. የስፖርት ምክር ቤት ዓመታዊ በጀት

5.6.1. የስፖርት ምክር ቤቱ ዓመታዊ በጀት ለአንድ ዓመት በምክር ቤቱ የፀደቀ በጀት ነው፣

5.6.2. የስፖርት ምክር ቤቱ የበጀት ዓመት ከመስከረም 1 ቀን እስከ ጳጉሜ 5 ወይም 6 ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል፣

5.6.3. የስፖርት ምክር ቤቱ ዓመታዊ በጀቶች የገቢና ወጪ በጀቶች ተብለው ይታወቃል፣

5.6.4. በስፖርት ምክር ቤቱ ለተለያዩ ስራዎች ከፀደቀው በጀት የተረፈው ገንዘብ ወደ ስፖርት ምክር ቤቱ ሂሳብ ተመላሽ ይሆናል፡፡

## 5.7. የስፖርት ምክር ቤቱ የወጪ በጀት

5.7.1. ለስፖርት ስልጠና ወድድርና ፌስቲቫል ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ፣

5.7.2. ለስፖርት ትጥቅ መሳሪያዎች ግዥ፣

5.7.3. ለሽልማትና ለሽልማት እቃዎች ግዥ፣

5.7.4. ለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ዕድሳትና ጥገና፣

5.7.5. ለስፖርት ምክር ቤቱ አስተዳደራዊ ወጪዎች፣

5.7.6. እንደ አስፈላጊነቱ ለምክር ቤቱ ስራ ለሚቀጠሩ ሠራተኞች ደመወዝ ወጪዎች፣

5.7.7. ለሌሎች ለስፖርት እድገት ወሳኝ የሆኑ ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

## 5.8. በጀት ስለማፀደቅ

5.8.1. በስፖርት ምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠቃሎ የሚቀርበው የየዓመቱ በጀት ለስፖርት ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ከፀደቀ በኃላ በስራ ላይ ይውላል፣

5.8.2. የየዓመቱ በጀት ለስፖርት ምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ እስኪፀድቅ ድረስ ስራዎች የስፖርት ምክር ቤቱ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተሰብስቦ ለአስቸኳይ ጉዳዩች በጀት በታሳቢ ሊፈቅድ ይችላል፣

## 5.9. የሂሳብ ሪፖርት ስለማቅረብ

5.9.1. የስፖርት ምክር ቤቱ የሂሳብ እንቅስቃሴ ሪፖርት በቢሮው ክፍያና ሂሳብ ዳይሬክቶሬት እንዲሁም በክ/ከተማና በወረዳ በክፍያና ሂሳብ ቡድን ተዘጋጅቶ በስራ አስፈፃሚ ታይቶ መፅደቅ ይኖርበታል፡፡

5.9.2. የስፖርት ምክር ቤቱ የሂሳብ እንቅስቃሴ ሪፖርት በስራ አስፈፃሚ ከጸደቀ በኂላ ከበጀት አመቱ የስራ ዕንቅስቃሴ ሪፖርት ጋር ተዘጋጅቶ ለጉባኤ ይቀርባል፡፡

## 5.10. የስፖርት ምክር ቤቱ የሂሳብ ምርመራ

5.10.1. በውጪ ኦዲት ይመረምራል፣

5.10.2. ምክር ቤቱ በሚሰይማቸው ኦዲት ኮሚሽን ኦዲተር አማካኝነት ይመረመራል፣

# ክፍል ስድስት

## 6. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 6.1. የስፖርት ምክር ቤቱ የሚከተሉት የህግ ሰውነት ይኖረዋል

6.1.1. የመክሰስና የመከሰስ መብት፣

6.1.2. ውል የመዋዋል፣

6.1.3. ሀብት የማፍራትና ንብረት የማስተዳደር፣

6.1.4. በገንዘብና በዓይነት የሚገኝ ገቢ የማሰባሰብ፣

### 6.2. ከምክር ቤት አባልነት ስለመሰናበት

6.2.1. ማንኛውም የስፖርት ምክር ቤት አባል በራሱ ፈቃድ ወይም የስፖርቱን መመሪያ የሚፃረር ተግባር በመፈጸሙ ምክንያት ከምክር ቤት አባልነት ሊሰናበት ይችላል፣

### 6.3. መመሪያ ስለማሻሻል

6.3.1. ይህ መመሪያ እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ የስፖርት ምክር ቤቱ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ሲጠይቁና በአባላቱ 2/3ኛ ድምፅ ሲደገፍ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል፣

6.3.2. እንዲሻሻል የቀረበው መመሪያ በአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ሲታመንበትና በፕሮሰስ ካውንስል ቀርቦ ሲፀድቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

### 6.4. መመሪያውን የማክበር ግዴታ

6.4.1. ማናቸውም የስፖርት ምክር ቤቱ አባላት ይህንን መመሪያ የማክበርና በስራ ላይ የማዋል ግዴታ አለባቸው፡፡

### 6.5. የተሻሩ መመሪያዎች

6.5.1. ይህን መመሪያ የሚቃረኑና ከዚህ በፊት በስፖርት ምክር ቤቱ ወጥተው የነበሩ መመሪያዎች በሙሉ በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

### 6.6. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

7. ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ም/ቤት 22/03/2015 ዓ/ም ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አቶ በላይ ደጀን**

**የአዲስ አበባ ስፖርት ምክር ቤት ም/ሰብሳቢ**